**የሕዝብ ተወካይ ራስኪን ባለብዙ ቋንቋ የህይወት ታሪክ እና የዲስትሪክት ጽሕፈት ቤት የእውቂያ ቅጽ**

## [በአማርኛ ቋንቋ]

### ስለ የሕዝብ ተወካይ የተከበሩ ራስኪን

ኮንግረስማን Jamie Raskin (ጄሚ ራስኪን) U.S. House of Representatives (በዩኤስ የተወካዮች ምክር ቤት) ውስጥ የሜሪላንድን 8ኛ Congressional Districtን (ኮንግረስ ዲስትሪክትን) በኩራት ይወክላሉ። ዲስትሪክቱ በአብዛኛው የMontgomery County (የሞንትጎመሪ ካውንቲ) እና የPrince George County (የፐሪንስ ጆርጅ ካውንቲ) አነስተኛ ክፍልን ያካትታል። ኮንግረስማን Raskin (ራስኪን) ጃንዋሪ 6 ቀን፣ 2023 ዓ.ም ላይ በተደረገው በ118ኛው ኮንግረስ መጀመሪያ ስብሰባ ላይ ለአራተኛ የምርጫ ጊዜ በመመረጥ ቃለ መሃላ ፈጽመዋል።

የሕዝብ ተወካይ የሆኑት Raskin (ራስኪን) በ Democratic Caucus (በዲሞክራቲክ ካውከስ) በ118ኛው ኮንግረስ ስብሰባ ላይ የምክር ቤቱ የበላይ ቁጥጥር እና የተጠያቂነት ኮሚቴ የደረጃ አባል በመሆን ተመርጠዋል። የበላይ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ ዓባል ሆነው ሲመረጡ ይኼ አራተኛ ጊዜያቸው ነው።

ከዚህ ቀደም የተከበሩ የሕዝብ ተወካይ Raskin (ራስኪን) በምክር ቤቱ የፍትህ ኮሚቴ እና በምክር ቤቱ የአስተዳደር ኮሚቴ ውስጥ ሶስት የምርጫ ጊዜ ያህል አገልግለዋል። በደንቦች ኮሚቴ እና የኮሮና ቫይረስ የተመረጡ ንዑስ ኮሚቴ ዓባል በመሆን ሁለት የምርጫ ጊዜ ላይ አገልግለዋል። በ117ኛው ኮንግረስ፣ የሲቪል መብቶች እና የዜጎች ነፃነቶች የቁጥጥር ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን አገልግለዋል። የተከበሩ የሕዝብ ተወካይ Raskin (ራስኪን) በቀድሞው ፕሬዝዳንት Donald Trump (ዶናልድ ትራምፐ) ሁለተኛው የክስ ችሎት ውስጥ ግንባር ቀደም የክስ ማናጀር ከመሆን በተጨማሪ ጃንዋሪ 6 በUnited States Capitol (በዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል) ላይ የደረሰውን ጥቃት ለመመርመር በተመረጡት ኮሚቴ ውስጥ አገልግለዋል።

የምክር ቤት ቆይታቸው ከመጀመሩ በፊት፣ Raskin (ራስኪን) በMaryland (ሜሪላንድ) ውስጥ የሶስት የምርጫ ጊዜ ያህል የግዛቱ ሴናተር ነበሩ፣ እዚያም የSenate Majority Whip (የሴኔት ማጆሪቲ ዊፕ) በመሆን አገልግለዋል። የጋብቻ እኩልነትን፣ የሞት ቅጣትን ማስቀረት፣ የቀድሞ እስረኞችን የመምረጥ መብት መመለስ፣ በአሜሪካ ውስጥ የመጀመሪያው የጥቅማጥቅም ኮርፖሬሽን ህግ መፅደቅ እና የብሔራዊ ታዋቂ ድምጽ ኢንተርስቴት ስምምነትን ጨምሮ በአናፖሊስ ውስጥ ጥምረቶችን በመገንባቱ የተከታታይ ድንቅ የህግ ስኬቶችን ለማቅረብ መልካም ስም አትርፏል American University's Washington College of Law (በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የዋሽንግተን የሕግ ኮሌጅ) ውስጥ የሕገ መንግሥት ሕግ ፕሮፌሰር በመሆን ከ25 ዓመታት በላይ አገልግለዋል። ብዙ መጽሐፍቶችን አሳትመዋል፣ ከእነዚህም ውስጥ በዋሽንግተን ፖስት ውስጥ በብዙ ቅጂ የተሸጡ መጽሐፍት በመባል የተሰየመው *Overruling Democracy: The Supreme Court versus the American People (ኦቨር ሩሊንግ ዲሞክራሲ፦ ዘ ሱፐሪም ኮርት ቨርሰስ ዘ አሜሪካን ፒፕል)*፣ ከፍተኛ እውቅና ያተረፈው *We the Students: Supreme Court Cases For and About America's Students (ዊ ዘ ስቱደንትስ፦ ሱፕሪም ኮርት ኬዝስ ፎር ኤንድ አባውት አሜሪካስ ስቱደንትስ)*፣ እና የኒው ዮርክ ታይምስ ቁጥር 1 በብዙ ቅጂ የተሸጡ መጽሐፍት አካል የሆነው *Unthinkable: Trauma, Truth and the Trials of American Democracy (አንቲንክብል: ትራውማ፣ ትሩዝ ኤንድ ዘ ትሪያል ኦፍ አሜሪካን ዲሞክራሲ)* ይገኙበታል።

ኮንግረስማን Raskin (ራስኪን) የHarvard College (የሃርቫርድ ኮሌጅ) እና የHarvard Law School (የሃርቫርድ የህግ ትምህርት ቤት) ተመራቂ ሲሆኑ Harvard Law Review (የሃርቫርድ ሎ ሪቪው) መጽሔት የቀድሞ አርታኢ ነበሩ።

## እገዛ ይፈልጋሉ? የእኔን ዲስትሪክት ቢሮ ያነጋግሩ።

የፌደራል ኤጀንሲ እርዳታ ከፈለጉ፣ የኮንግረስማን Raskin (ራስኪን) ሰራተኞች ችግር መፍታት ላይ ሊያግዙት ወይም የሚፈልጉትን መረጃ ሊሰጥዎት ይችላሉ። ለችግርዎ ፍትሃዊ እና ወቅታዊ ምላሽ እንዲያገኙ ለማገዝ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን።

ከቢሮአችን እርዳታ ለማግኘት መጀመሪያ የግል መረጃ ፍቃድ መስጫ ቅጽ መሙላት፣ መፈረም እና ለቢሮአችን የተሞላውን ቅጽ መልሰው ማስገባት አለቦት። የተሟላ የግል መረጃ ፍቃድ መስጫ ቅጽ ለማስገባት እባክዎ ከታች ከተዘረዘሩት አማራጮች ውስጥ አንዱን ይምረጡ።

## አንላይን የሚሞላ ቅጽ

[አንላይን ፓርታሉን ለመጠቀም እዚህ ጋ ጠቅ ያድርጉ።] ተገቢውን ቅጽ ከማንኛውም ደጋፊ ሰነዶች ጋር በማያያዝ በዲጂታል ፊርማ በመፈረም ለቢሮአችን ማስገባት ይችላሉ።

## በኢሜይል የሚሞላ ቅጽ

ተገቢውን የግል መረጃ ፍቃድ መስጫ ቅጽ ይሙሉ፣ ይፈርሙበት እና በዚህ ኢሜይል አድራሻ ላይ ይላኩት Raskin.Casework@mail.house.gov

- የግል መረጃ ፍቃድ መስጫ ቅጽ ለሁሉም የኢሚግሬሽን ላልሆኑ ጉዳዮች (ማህበራዊ ደህንነት፣ Medicare (ሜዲኬር)፣ IRS (አይአርኤስ)፣ የቀድሞ ሠራዊት ዓባላት ጉዳይ፣ OPM (ኦፒኤም)፣ ወዘተ።) - እዚህ ጋ ጠቅ ያድርጉ
- ለኢሚግሬሽን ጉዳዮች (የስቴት ዲፓርትመንት ወይም USCIS) የግል መረጃ ፍቃድ መስጫ ቅጽ- እዚህ ጋ ጠቅ ያድርጉ
- ለኢሜግሬሽን እና የጉምሩክ ማስፈጸሚያ (Immigration and Customs Enforcement, ICE) ጉዳዮች ብቻ የሚውል የግል መረጃ ፍቃድ መስጫ ቅጽ - እዚህ ጋ ጠቅ ያድርጉ

## በደብዳቤ የሚላክ ቅጽ

ተገቢውን የግል መረጃ ፍቃድ መስጫ ቅጽ በወረቀት ፕሪንት በማድረግ፣ ይሙሉት እና ይፈርሙበት። በሚከተለው አድራሻ ላይ በቀጥታ ለዲስትሪክት ቢሮ ይላኩ፡- 51 Monroe St, Suite 503, Rockville, MD 20850።

- የግል መረጃ ፍቃድ መስጫ ቅጽ ለሁሉም የኢሚግሬሽን ላልሆኑ ጉዳዮች (ማህበራዊ ደህንነት፣ Medicare (ሜዲኬር)፣ IRS (አይአርኤስ)፣ የቀድሞ ሠራዊት ዓባላት ጉዳይ፣ OPM (ኦፒኤም)፣ ወዘተ።) - እዚህ ጋ ጠቅ ያድርጉ
- ለኢሚግሬሽን ጉዳዮች (የስቴት ዲፓርትመንት ወይም USCIS) የግል መረጃ ፍቃድ መስጫ ቅጽ- እዚህ ጋ ጠቅ ያድርጉ
- ለኢሜግሬሽን እና የጉምሩክ ማስፈጸሚያ (Immigration and Customs Enforcement, ICE) ጉዳዮች ብቻ የሚውል የግል መረጃ ፍቃድ መስጫ ቅጽ - እዚህ ጋ ጠቅ ያድርጉ

## የዲስትሪክት ቢሮ የማነጋገሪያ መረጃ

51 Monroe St, Suite 503
Rockville, MD 20850

ስልክ፡- 301-354-1000